# የትም አትጠብቂኝ

**ሰለሞን ሽፈገራው**

… እናም ይሄውልሽ፣ እኔ ማለት ይህ ነኝ…!
የዘመነ "ፌዝ ቡክ" ምኞት ቀልቤን ነስቶ-
እያብከነከነኝ፣
የማላውቀው አገር ፣ ናፍቆት ሲያመንነኝ፣
ዓይኔ ሥርያለውን፣ ድንግል ውበት ድምቀት -
ማየት የተሳነኝ…
እኔ ማለት ይህነኝ፣ እንደ አለመታደል፣
በፈረንጅ "በርገር፣" ከርሴን ለማጠብደል፤
ጥራዝ በነጠቅኩት፣ የእንግሊዝ አፍ ፊደል
ከዘመነ "ፌዝ ቡክ" ዓለም ጋር ስዳለል…
ሥልጣኔ ማለት፣ ጥሮ ግሮ ማትረፍ ፣
ሰጥቶ መቀበል፣
የመሆኑ ምስጢር፣ የገባኝ ለመምሰል፤
እምነቴን እውነቴን፣ አንቄ የምገል፡፡
የሌሎች መሠልጠን፣ እኔን አስይጥኖ፣
ለከት ባጣ ምኞት፣ እየነሳኝ መቅኖ ፣
ቃልኪዳናችንን፣ በ"ፌዝ ቡክ" ገበያ
እንዳወጣ ሽጬ፣
"ሆሊውድ ቦሊውድ" ፣ በመንፈስ ልሰደድ
ባሕር አቋርጬ…
ልጅ ወልዶ የመሳም፣ ተስፋሽን ላጨልም፣
አውሮፓን ስናፍቅ ፣ አሜሪካን ሳልም፤
የዘመነ "ፌዝ ቡክ" ምኞት ቀልቤን ነስቶኝ፣
የ"ኦፕራ" አድናቆት፣ የ"ማዶና" ቅብጠት፣
መንገዴን አስቶኝ፣
ዘወትር ሌት ተቀን፣ ካንቺ በስተጀርባ፣
"አንጀሊና ጆሊን" ፣ አጭቼ ላገባ፣
በመንፈስ "ሆሊውድ" ፣ ሂጄ ጡት ስጣባ…
ታቦትም ጣዖትም ፣ ማምለክ እስኪያቅተኝ፣
የማላውቀው አገር ፣ናፍቆት ሲያቃትተኝ፣
ውቂያኖሱን ገምሶ፣ እንደበትረ ሙሴ፣
ካትላንቲክ ባሻገር፣ ሲሰደድ መንፈሴ …
እናም ይኸውልሽ፣ እንደአለመታደል፣
በፈረንጅ በ'ርገር'፣ ከርሴን ለማጠብደል፣
እምነቴን፣ እውነቴን፣ አንቄ በመግደል፣
ከዘመነ 'ፌዝ ቡክ' ዓለም ጋር ስዳለል፣

የ"ቢዮንሴ" ናፍቆት፣ የ"ሻኪራ" አድናቆት፣
እያብከነከነኝ፣
ዓይኔ ሥር ያለውን፣ ቀንዲል ውበት ድምቀት
ማስተዋል ሲሳነኝ፣
ምን አለብትንቂኝ?
ግዴለም ልቅርብሽ፣ ሳርቅሽ እራቂኝ…!
ፒያሳ ማሐሙድጋ፣ ወይም ቦሌ "ፒኮክ"፣

እንዳትጠብቂኝ፡፡
ለፍተው ጥረው ግረው፣ ለተግባር ሳይሰንፉ፣
በየዘመናቱ፣
ቅድመኩሉ ዓለም፣ ምስጢረ ሕላዌን፣
መርምረው የፈቱ፣
የብሉይ የሀዲስ፣ አበው ሊቃውንቱ፣
ከሺህ ዘመን ታሪክ፣ ጉዞ ውጣ ውረድ
በደም ባጥንታቸው፣ ውህደት የነደቁት፣
የማንነት ዓጸድ፣
ኢትዮጵያዊነት፣ ውሉ እንዳይንጋደድ፣
ለራሰ ውበት ድምቀት፣ ለቀየው ላድባሩ፣
ጸድቃን በፍቅራቸው፣ ለባረኩት ምድር፣
ለየ ሽንተረሩ ፣
የካምቅዱስ መንፈስ፣ ላረፈበት ጫካ
ላጋም ለግራሩ፣
በፍፁም ልባቸው፣ ታምነው እየኖሩ፣
ዓርብ ሮብ ሁዳዴን፣ ፆም ጸሎት ሳይገድፉ፣
ለደርቡሽ ቅዝምዝም፣ አንገት እየሰጡ
እንደተሰየፉ፣
ያውሮፖ "ፋሽዝም"፣ ባዘነበባቸው፣
ጅምላ ጨራሽ ዶፉ፣
አብረው ተነባብረው፣ እንደመፀው ቅጠል
ባንድ እየረገፉ፣
በሰው ዘር ታሪክ ፊት፣ ለእናት ሀገር አምላክ
ታምነው እንዳለፉ…
የብሉይ የሀዲስ፣ ቅም አያቶቻቸው…
አንደኩሽ እንደሴም፣ በረከት ቀርቧቸው፣
የኖህ የበኩር ልጅ፣ የካም ቅዱስ መንፈስ
አድሮ በውስጣቸው…
እንኳንስ ደጋግመው፣ ያዩትን በውኑ፣
ከዕለታት አንድ ቀን፣ የደብር አለቃው
አቡኑ-ካህኑ…
ወይ ደሞ ባሕታዊ "ያለምነገር በቃኝ "
ብለው ቆብ የጫኑ፣
ግሸን ደብረ ዳሞ፣ ዋልድባና ጣና
ገብተው የመነኑ፣
የገዳም መነኩሴ፣ የሰበኳቸውን
ሳያዩ እያመኑ…
የወሎው ዱበርቲ ፣ የሐረሮች ዱአ
እነ ሼክ አባድር፣
አሚሮች ሱልጣኖች፣ በቅንነታቸው
ከባረኳት ምድር…
አበው ደጋጎቹ ፣ጥንቱንም ሲጀመር ፣
እነ ሁሴን ጅብሪል ፣የባሌው ሶፍ ዑመር ፣
አሕመድ አልነጃሺ፣ ከማይመረመር፣
የልብ ቅንነት ፣በመነጨ ፍቅር፣
ነግሦ ዘውዱን ጭኖ፣ ከባረካት ምድር፣
እያንዳንዱ ዜጋ ፣ደጃፍ በሚበቅል
ደማከሴ ቅጠል
ጻድቃን በፍቅራቸው፤ በቀደሱት ውሃ
በሸንኮራ ፀበል፣

ከነፍስም ከሥጋም፣ ሕመም የሚድኑ፣
ዕልፍ አዕላፍ ብፀዓን፣ በየማዕዘኑ ፣
ካሉበት ኢትዮጵያ፣ ከቅድስት አገሬ ፣
አንድ ነጭ አምላኩ፣ ሃጥእ ተፈጥሬ ፡፡
እምነቴን እውነቴን፣ እንደተራ ሸቀጥ
ባሕር አሻግሬ፣
ለማንም ለምንም፣ ልሸጥ- ልለውጠው
ላጠፋው መንዝሬ፣
"ሆሊውድ- ቦሊውድ፣" ሲሆን ውሎ አዳሬ፣
ከገዛ ራሴ ጋር ፣ሰኳረፍ አምርሬ...
ከንቱነቴን ዓይተሽ፣ ብትንቂኝ ምን አለ?
በግሎባልዘመን ፣ለከት የለሽ ቅንጦት
ቀልቡ እየማለለ፣
ከድፍን ዓለም ጋር፣ በ"ፌዝ ቡክ" ገበያ
እንደተዳለለ፣
ለ"ማዶና" አድናቆት፣ ለቢዮንሴ ናፍቆት፣
ደጅ አድሮ እየዋለ፣
የሰማኒያ ሚስቱን፣ ከጅብ ያላሰጣለ...
የአህያ ባል ቢጤ፣ መሆኔን ስታውቂኝ፣
ከንቱነቴን አይተሽ፣ ምን አለ ብትቂኝ ...!?
እምነቴን እውነቴን፣ እንደተራ ሸቀጥ፣
ለማንም ለምንም፣ ልሸጥ ልለውጠው
አሳልፌ ልሰጥ፣
በባሌም በቦሌም፣ ዳር ድንበር ላቋርጥ፣
የምዕራቡን ዓለም፣ በምኞት ስቋምጥ...
ሀገሬን ወገኔን፣ ለቀን ጅብ ሰጥቼ፣
አንቺንም እዚሁ፣ ባለሽበት ትቼ፣
እኔ ግን በመንፈስ፣ ሰርክ ነጋ ጠባ፣
ጧትም ማታም ሌትም ...
በ"ፌዝ ቡክ" ስሰደድ ፣ ስጓዝ ወደ የትም...
እምነቴን እውነቴን፣ አንቄገድዬ፣
ወልዶ ካሳደገኝ፣ ቅዱስ አድባር ቀዬ፣
ከራስ ሀገር ወገን፣ መሀል ተነጥየ ፣
በፈረንጅ በ"ርገር"፣ ከርሴን ላጠበድል፣
ዘወትር በመንፈስ፣ ኃይት ሃውስ ደጃፍ
ዲሲ ሳውደለድል፣
የሌሎች መሠልጠን፣ እንደ አለመታደል
እኔን አሰይጥኖኝ፣
ይህ ግሎ ባልዘመን ፣ ለከት ባጣ ምኞት
እያብከነከነኝ
የማለውቀው አገር ፣ናፍቆት ሲያመንነኝ
ዓይኔ ስር ያለውን፣ ቀንዲል ውበት ድምቀት
ማየት የተሳነኝ...
ያንቺን ንፅህና ፣የፍቅርሽን ጥልቀት፣
በማይመረመር፣ ልባዊ ቅንነት፣
ያጠባበቅሽውን ፣የተሰፋ መቀነት፡፡
የእምነትሽን ፅናት፣ አላውቀው ይመስል፣
ንፁህ ልቦናሽን፣ በክህደት ላቆስል፣
የ"ማዶናን" ቅብጠት፣ ከሩቅ ሳብሰበለሰል፣
በመንፈስ "ሆሊውድ፣" ወለም ዘለም ስል፣
መሠልጠን ቢያቅተኝ፣ ወሲብ ለመኮረጅ፣

ምግባር የጎደለው፣ ጋጠ ወጥ ፈረንጅ፣
የማገጠበትን 'አንላይን' ሰጎመጅ…
እምነቴን እውነቴን፣ አንቄ ልገድል፣
አሜሪካን ሳልም፣ አውሮፓን ስማልል፣
የሰማኒያ ሚስቴን፣ ከጅብ የማላሰጥል፡፡
የአሀያ ባል ቢጤ፣ መሆኔን ስታውቂኝ
እባክሽ ከእንግዲህ፣ የትምአት ጠብቂኝ…!
ከንቱነቴን አይተሽ ምን አለብትንቂኝ…?
ሥልጣኔ ማለት፣ በራስ ቀንዲል እውነት
ጥሮ ግሮ ማትረፍ፣
ለወገን የሚበጅ፣ ዕውቀት መጎናጸፍ
በራስ ጥቡብ መድመቅ፣ ምዕዋትን መጠየፍ…
ሥልጣኔ ማለት፣ ለራስ ታምኖ መኖር፣
የድንግል ተፈጥሮን፣ ዑደት በመመርመር፣
ምስጢረ ሕልዌን፣ በስሌት መቀመር፣
በራስ ውበት ድምቀት፣ ሕይወትን ማሳመር፣
ሥልጣኔ ማለት፣ አዲስ ነገር መፍጠር፡፡
የገሀዱን ዓለም፣ በጥልቀት መገንዘብ፣
ወልዶ ላሳደገ ፣የራስ ኀብረተሰብ፣
ለራስ ሀገር ወገን፣ አበክሮ ማሰብ፣
እንደሆነ ፍቺው ፣መሥልጠን የሚሉት
ዘመናዊ ዘየ.
ምኑም እያልገባኝ፣ የገባኝ መስየ፣
ከራስ እናት ሀገር፣ አድባር አውጋር ቀዬ፣
ከተሰፋይቱ ምድር፣ ኀብረ ብዙ ሕዝቦች፣
በመንፈስ ስነጠል፣
ለራስ ቤት ነጻነት፣
አበው ከሞቱለት፣ እምነት ሰገነጠል…
በደም ባጥነታቸው፣ ውህደት ከነደቂት፣
የማንነት ዓጸድ፣
ከራስ ሕያው እርስት፣ እርቄ ልሰደድ፣
በ"ፌዝ ቡክ" ጎዳና፣ ወደ የትም ስሄድ
ካንጅት ለሚወዱት፣ የቅርብ ወዳጅ ዘመድ…
የዕንቁጣጣሽ ሰሞን፣ አዲስ ዘመን ጠብቶ
ዓዳይ ሲፈነዳ፣
ልክ እንደመስቀል ወፍ፣ ዓመት  ሙሉ ጠፍቶ
ለሚመጣ እንግዳ፣
በስስት ተቀጥፎ ፣ከማሽላው ዘላ፣
ከሚወዱት ሰው ጋር፣ ላምሮት ያህል ብቻ
ታሽቶ እንደሚበላ፣
እንደውልብኝ እሸት፣ በትኩሱ ሳይበርድ፣
እንብዛም ሳይጠቁር፣ እንብዛም ሳይቀላ
በደርዝ የሚገመድ …
ኩልል ጥልል ያለ፣ እንደጸደይ ሰማይ፣
ጠይም ፀዳል ውበት፣ ኢትዮጵያዊ ላህይ፣
እንብዛም ሳይጠቁር፣ እንብዛም ሳይቀላ፣
ሁለቱ መሀል ላይ…
ዓይኔ ሥር ያለውን፣ ያንቺን ቅዱስ ገላ
ማየት የተሳነኝ ፣
እንደ አለመታደል፣ እኔ ማለት ይህ ነኝ፡፡
በራስ ቀንዲል ጥበብ፣

በግዕዝ በዕዝል ድፋት ወአራራይ
እሳትና ውሃ አፈርና ነፍስ
ተስማምተው አንድ ላይ፣
ምስጢረ መለኮት በሚገለፅበት
ያሬዳዊ ዜማ
ቢላልአል ሐበሽ ቅድሙ ኩሉ ዓለም
በቃኘው መንዙማ…
የተሰነፋይቱን ምድር፣ ሰም እያወደሱ፣
ከብሉይ ከሀዲስ ፣የቅድስናዋን
ምንጭ እያጣቀሱ፤
የሺህ ዘመን ታሪክ፣ ገድል እያወሱ…
ለራስ ሀገር አምላክ፣ ቅኔ ማኅሌት ቆመው
ለሊት ሲቀድሱ፤
ሳይተኙ እያደሩ፣ ቀን ጠምደው
የሚያርሱ…
ቅድመ ኩሉ ዓለም፣ ቢላል በአዛኑ
ላስመረላቸው ሰላት፣ የታመኑ
ዕልፍ አዕላፍ፣ ብጹአን በየማዕዘኑ፣
ይሄው ዛሬም ፣ድረስ ካሉባት ሀገሬ፣
እንደ አለመታደል ፣አንድ ነጭ አምላኩ
ሃጥእተፈጥሬ…
እምነቴን እውነቴን፣ እንደተራ ሸቀጥ
ባሕር አሻግሬ፤
ለማንም - ለምንም፣
ልሸጥ ልለውጠው ፣ሳጠፋው መንዝሬ፣
“ሆሊውድ ቦሊውድ” ፣ ሲሆን ውሎ አዳሬ…..
ሳገር በቀሉ ዛፍ ፣ለዋርካው ለዝግባው
ለዋንዛ ለሾላ…
እንዳባቶቻቸው፣ ለራስ ቤት ነጻነት
ሀጃ የሚሞላ
ሸንጎ ተቀምጠው፣ በሚመቱት መላ፣
ቅን ለሚመክሩበት፣ከደጋ እስከ ቆላ፣
ለየደጃፋቸው ፣ግራዋና ፊላ፣
ላረንጓዴው ውበት፣ ለዛፉ ለግንዱ
ለሣር ለቅጣሉ፣
ለወንዝ ለጅረቱ ፣ለዱር ለገደሉ፣
ካራቱም ማዕዘን፣ ክረምት ከበጋ
ቁልቁል ለሚፈሰው፣ የተሰፋይቱ ምድር
ተፈጥሯዊ ጸጋ…
ዛሬም እንደ ጥንቱ፣ ለአድባር-ላውጋሩ፣
በፍፁም ልባቸው ፣ታምነው እየኖሩ፣
ለአንድ እናት ሀገር፣ የየራሳቸውን
ታሪክ የሚሠሩ፣
ጥሮ አትራፊ ሕዝቦች ፣በቅንነታቸው
ከባረኩት ቀየ ፤
አንድ ነጭ አምላኩ ፣መናፍቅ በቅዬ…
እናም ይኸውልሽ፣ እንደ አለመታደል፣
እምነቴን እውነቴን፣ አንቂ በመግደል፣
የፈረንጅ “በርገር” ፣ ጠግቤ ለመብላት
(ከርሴን ለማጠብደል)፣
በ ’ፌዝ ቡክ’ ገበያ፣ ከግሎባል ዘመን

ዓለም ጋር ስዳላል፤
የሌሎች መሠልጠን ፣እኔን አሰይጥኖ፣
ሆሊውድ ቦሊውድ፣ በተሰኘው ምትሃት፣
እየነሳኝ መቅኖ ፤
ዓይኔ ሥር ያለውን ፣ቀንዲል ውበት ድምቀት
ማየት እስኪሳነኝ ፤
የማላውቀው አገር ፣ናፍቆት ሲያመንነኝ…
በ“ግሎባል” ዘመን ፣ለከት የለሽ ምኞት
ከሚያብከነክነኝ፤
ከ’ፌዝ ቡክ’ ልክፍቴ፣
የቄሱም የሼኩም ፣ጸሎት ካላዳነኝ…፣
ከንቱነቴን ዐይተሽ፣ ምን አለ ብትንቂኝ?
ግዴለም ልቅርብሽ ፣ይገፄሽ እንዳልጠፋ
አምርረሽ እራቂኝ፡፡
ፒያሳ መሐመድጋ ፣ወይም ቦሌ ፒኮክ
የትም አትጠብቂኝ…!
አክ እንትፍ! አክ እንትፍ! አክ እንትፍ! ብለሽ
ከልቦናሽ ፋቂኝ!!

*ሰለሞን ሽፈራው*

*የዴያስፖራ ፖለቲከኞችን ምጽኣት በመጠበቅ ለተጠመዱና አገር ቤት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ማስተዋል ለተሳናቸው ወገኖቼ*

*ህዳር 2005ዓ.ም አዲስ አበባ*